# ወያኔ ለምኔ!

በወርሃ ግንቦት ብዙ ነገር ታይቱዋል፣
ገንጣይ ከፋፋይም ሀገር ተቆጣጥሩዋል።
ሕዝብ እየጠበቀ ፍትህ በጉጉት፣
ወያኔዎች ገብተው ስቃይ አሳዩት።
ምርጫኣን አጭበርብሮ ኮሮጆ መድፋት፣
እንደ ብልጠት ወስዶ ብዙ መደንፋት፣
ጊዜው ይደርስና ያስደፋል አንገት።
ሕዝብን መከፋፈል በዘር በሃይማኖት፣
ለሃገር አይጠቅምም አያስገኝም እድገት።
ምን ፋይዳ ይኖረዋል፣ መማል መወሸከት፣
ተጨባጭ ውጤት ነው ለሕዝብ ማሳየት።
ምን ዋጋ ይኖረዋል ባዶ ቁጥር መደርደር፣
ሕዝብን አያሳምን አያስገኝም ክብር፣
ስለዚህ ይሻላል በወቅቱ እውነት መናገር፣
ከአቅም በላይ ሆኖ ሲያጋጥም ችግር።
እስቲ ተመልከቱ አስቡ እንደሰው፣
ጊዜው ለእውነት እንጂ ለውሸት ቦታም የሌው።
ምንም ሃይል ቢበዛ ሃብት ቢትረፈረፍ፣
ሊሸፍን አይችልም የአይምሮን ጉድፍ።
ትንሽ መለስ ብለን ብናይ ወደሁዋላ፣
ይሄ እርም የማያውቅ ስንቱን ወገን በላ!
ብዙ ሰው ካለቀ በዚህ የሰው አውሬ፣
መድሃኒት እንፈልግ ሳንል ነገ ዛሬ።
መሳሪያ ደግኖ ሕዝብ ከሚገዛው፣
ከአለም ዲክታተሮች ወያኔ አንዱ ነው።
ትቢት የመውደቂያ ምልክት ነው፣
   ስለዚህ የሕዝብ አሰቃዮች፣
አይምሮ ካላቹሁ ካሁኑ ማሰብ ነው።
ሕዝብ አቁዋሙን ገልጹዋል ምሎ በሰላሴ፣
መቼም አይገባችሁ እነስልጣን ነፍሴ።
ሃገር ሲቆራርስ ሆኖ፣የውጪ ምስለኔ፣
ወገኔን ሲጨርስ በርሃብ በጠኔ፣
ውሸት ሲደረድር ብሎ ለስልጣኔ፣
ምን ሊፈይድልኝ ነው ወያኔ ለምኔ።
ስለዚህ ተነሳ እምቢበል ወገኔ፣
ማለት ይጠቅምሃል እምቢ ለወያኔ።

ይበልጣል እውነቱ   ከጀርመን።

ግንቦት 2001
May 2009